ትምህርት እና የስብእና እነፃ

ቀደም ብለን እንደጠቀስነው ሰላሑዲን የልጅነት ጊዜውን ያሳለፈው በዕለበክ ውስጥ ነበር። ይሁን እንጂ አንድ ቦታ ተቀምጦ የመማር ዕድል ወይም አጋጣሚው ስላልነበረው ከአንድ ከተማ ወደ ሌላ ከተማ በመዘዋወር ተማረ። ሳላሑዲን በጊዜው እንደነበሩት እንደማንኛውም የከፍተኛው ማህበራዊ መደብ መስለም ልጅች ማንበብና መፃፍ ለመማር፣ ቁርአን ለመሐፈዝና የአረብኛ ሰንቋ ህጎችን ለማጥናት ሁኔታዎች ተመቻችተውለት ነበር።

የ ‹ጦበቃት አሽ-ሻፊዓያ› ደራሲ ሳላሑዲን ከሐፊዝ አል-ሠለፊ ኢብን ዓውፍ አል-ናይሳቡሪይ እና አብዱላህ ኢብን ባሪ ዘንድ ሐዲስ ተምሯል በማለት ዕፊዋል። ሰላሑዲን ህግ አዋቂ፣ በተጅዊድ (ሥነ-ቁርአን አነባብ) ቁርአን አንባቢ እና ከልቡ ገጣሚ ነበር።

ከምስራቅና ከምዕራብ አትጣጫዎች፣ ከሰመርቀንድ እና ከኮርዶቫ ከተማዎች በርካታ ምሁራን በመስጂዶችና በትምህርት ቤቶች ውስጥ ለመማርና ለማስተማር ወደ ደማስቆ ይጎርፉ እንደነበር ሁሉም የታሪክ ሀሐፊዎች በአንድ ድምፅ ይገልፃሉ። በዕርግጠኝነት ሰላሑዲን ከአብዮኖቹ ምሁራን ተምሯል። በተለይ በኑረዲን ግብገፆ ወደ ደማስቆ በመምጣት በደማስቆና በሌሎች የተለያዩ የሶሪያ ከተማዎች[3] ትምህርት ቤቶችን ከገነቡት እና በአል-አመዊ መስጅድ ውስጥ ያስተምሩ ከነበሩት ከአብዱላህ ኢብን አቡ አስረን ተምሯል። በወቅቱ አቢ-አስረን የደማስቆ ዳኞች ፍርድ ቤቶች ፕሬዝዳንት ለመሆን በቅተው ነበር። ሰላሑዲንም እኚህን ሊቅ በጣም ያከብራቸውና ይንከባከባቸው ነበር። በተለይ የአይኖቻቸውን ብርሃን ባጡ ጊዜ እጅግ ተንከባክቧቸዋል።

ሰላሑዲን በፈረስ ግልቢያ፣ በጦር ውርወራ፣ በአደንና በወታደራዊ ጥበባት የላቀ ችሎታ በነበራቸው አካባቢዎች መኖሩ በእነዚህ መስኮች

---

[3] በመዕሀፉ ውስጥ ‹ሶሪያ› እና ‹ታላቋ ሶሪያ› የሚሉት ስሞች ዛሬ ሊባኖስ፣ ፍልስጤም፣ ዮርዳኖስ እና ሶርያ ብለን የምንጠራቸው አገሮች የያዟቸውን ቦታዎች በሙሉ አጠቃለው እንደሚገልፁ ማስታወስ እንወዳለን። በዚያ ጊዜ አካባቢው ‹ሻም› ተብሎ ይጠራ ነበር። ነገር ግን ዛሬ ‹ሻም› የሚለው መጠሪያ ደማስቆን በመግለፅ ብቻ ጥቅም ላይ ውሏል። (አዘጋጁ)

ላይ የተካነ እንዲሆን ረድቶት ነበር። በመሆኑም ልምዱን በማዳበር ሠራዊቱን መምራት ችሎ ነበር። በጦርነት ውስጥ የሚፈጠሩ አስቸጋሪ አጣብቂኞችን በቀላሉ ይፈታቸው ነበር። በተጨማሪም ታላቅ ተዋጊ ለመሆን የሚያበቁ አዕምሯዊ አትም፣ የመገንዘብ ችሎታ፣ አካባቢ፣ ስልጠና እና ትምህርት የመሳሰሉ መሠረታዊ ነገሮች ተሟልተውለት ነበር። ብዙ ጊዜ እነዚህን ሁሉ ነገሮች በአንድ ግለሰብ ላይ ተጠቃልለው ማግኘት ያስቸግራል።

ሌሎች ሰዎች በድንጋጤ አእምሯቸውን በሚስቱባቸውና የማገናዘብ አቅማቸውን በሚነጠቁባቸው አስፈሪ ጊዜያቶች የማሰብ ሚዛኑን መጠበቅ መቻሉና ዕኑ ልቡ ለትልቅ ስብዕና ያበቁት ሊሎች ባህሪዎቹ ነበሩ። ለምሳሌ ሶርያን የተቆጣጠሩ ጊዜ ወንድሙ ታጅ አል-መሉክ እንደተገደለ ተነግሮት ነበር። የ‹አክሬ›ን ጦርነት ካሸነፉ በኋላ ደግሞ የወንድሙንና የአል- ማሊክ አልማህፉዝን መገደል ሰማ። ሁለተኛው ወንድሙ ምሽጎችን በማደራጀት፣ በመከላከልና በመጠበቅ የተዋጣለት ኢንጂነር ነበር። ይሁንና እነዚህ ክፉ ዜናዎች በቀላይ ጦርነቶች ውስጥ ተዕፅኖ አልፈጠሩበትም ነበር።

ቀደም ብለን በጨረፍታም ቢሆን ካየነው የልጅነት ሕይወቱ በመነሳት ሰላሁዲን ብልህ ፖለቲከኛ፣ የዳበረ ልምድ ያለው መሪ፣ በሥርዓት የሠለጠነ ተዋጊ እና የላቀ ምሁር እንደነበር መረዳት እንችላለን። የሒጥቲን ጦርነት ድል አድራጊ እንዲሆን፣ በመስቀሎች ልብ ውስጥ ፍርሃት እንዲነግስ፣ ከምስራቅ እስከ ምዕራብ ዝናው እንዲናኝ፣ ለመጪዎቹ ትውልዶች መልካም አርዓያነትን እንዲያስቀምጥና ከታሪክ ታላላቅ ስብዕናዎች መካከል አንዱ ሆኖ እንዲመዘገብ ዕጣ ፈንታ እሱን የፈለገች ይመስል ነበር። እናቶች እንዴት ተሳናቸው!? ምንግዜም በሚቀጣጠል ፍላጎቱና ጀግንነቱ፣ የኢስላምን ጠንካራ ይዞታ፣ የነቢያትን ክብርና ደረጃ በመጠበቅና በመከላከል ሰላሃዲንን የሚመስል ሌላ ልጅ መውለድ እንዴት አቃታቸው! ያን ድንቅ ስብዕና ዳግም ቀርፆ ለዓለም ማበርከት ለምን ከበዳቸው።

ምዕራፍ ሁለት

የአስተዳደሩ መጀመሪያ

ግብፅ በሳጢማይድ ሥርወ መንግሥት ጊዜ

ሰላሐዲን ከመምጣቱ በፊት ግብፅ በአማፅያንና በመሾኮች፣ በቱርኮች፣ በሱዳናችና በሞሮኳዊያን በተደራጁ የተለያዩ ቡድኖች የእርስ በርስ ሽኩቻ ትታመስ ነበር።[4] ድህነትና ረሃብ አለትዮ ተስፋፍተው የህዝቡን ኖንካራ አድትቀውት ነበር። ኽሊፋቶችንና የሥርወ መንግስቱን የበላይ ገኘር ወይም አስተዳዳሪ (ወዚር) ለመግደል በተለያዩ መንገዶች ይደሰት ነበር።

የሳጢማዮቹ ኽሊፋ አገራቱን የሚቆጣጠርበት አቅም አልነበረውም። ፅውነተኛ ኃይል የነበረው ድል በቀናው ገኘር እና የጦር አበጋዝ እጅ ነበር። የገኘርነቱን ቦታ ለመያዝ በሚፈጠሩ ጥሎች ምክንያት ብዙ ደም አፋሳሽ ጦርነቶች ይካሔዱ ነበር። እ.ሐ.አ በ549 ጣላፅ ኢብን ሩዚቅ የሥርወ መንግሥቱ ገኘር በሆነበት ጊዜ አንዛራዊ መረጋጋት በፈጠርም እ.ሐ.አ 558 (እ.ኤ.አ 1163) ላይ ጠላፅ ተገድሎ በልጁ በሩዚቅ ኢብን ጣላፅ ተተካ። እንደገና ሁከት ነገሰ።

ኑረዲንና መስቀለኛው የየሩሳሊመ ንጉሥ አልማሪክ (በአረብኛ አል-አሙሪ) ለግብፅ የተለየ ትኩረት ነበራቸው። ሁለቱም በየበኩላቸው ግብፅን በመያዝ ኃይላቸውንና ግዛታቸውን ለማጠናከር የሚችሉትን ሁሉ ያደርጉ ነበር። አንዳቸው ሌላኛውን በፍርሃት ይመለከት ነበር። ይኸው ግብፅ ውስጥ የነበረው የገኘርነቱን ቦታ ለመያዝ የሚያረግ ሽኩቻ ኑረዲንን እና አል-ማሪክን በግብፅ የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ ለመግባት ጥሩ አጋጣሚ ፈጥሮላቸው ነበር።

---

[4] መሾኮች ከጦርነት የተማረኩ ወይም ከፐርሺያ፣ከማዕከላዊ እስያ እና ከሌሎች የባሪያ ንግድ የገበያ ቦታዎች ተገዝተው የመጡ ነጭ ባሪያዎች ነበሩ። መጀመሪያ ላይ ለውትድርና ይሰለጥኑ ነበር። ከህገቡ ጋርም አያቶላቱም ነበር የራሳቸውን ማንነት እንደጠበቁ ይኖሩ ነበር። (አዘጋጁ)

የሻዊር አስ-ሳዕዲ አመፅ

ሩዚት ኢብን ጠላዕ የፋጢሚዮች ዝሊፋ የበላይ ገዥ (ወዚር) ሆኖ ሥርወ-መንግሥቱን በሚመራበት ጊዜ የግብፅ የላይኛው ክፍል አስተዳዳር የነበረው ሻዊር ኢብን መ·ጂደር አስ-ሳዕዲ አምያበት· ነበር። እ.ሊ.አ በ558 በመ·ሐረም ወር ከሩዚት ጋር ጦርነት· ገጥሞ በማሸነፍና ሩዚትን በመግደል የገዥነቱን ቦታ መተካት· ችሎ· ነበር።

ሻዊርና ልጆቹ በሙስና በመዘፈቃቸው ምክንያት ከጅኔራሎቹ ውስጥ አንዱ የነበረው ዱር.ጋም ኢብን ዳሚር አላንካሚ ከፋጢሚዮች ዝሊፋ ጋር በመሆን ሻዊርን የሚያስወግዱበትን መንገድ መፈለግ ጀመሩ: : ዱር.ጋም በሻዊር ላይ እንዲያምፅ ዝሊፋው ግፊት አደረገበት። ሻዊር ነቁለለ። ዱር.ጋም የገዥነቱን ቦታ ያዘ። ወዲያውኑ· ፊቱን ወደ ደማስቆ አዞረ። በግብፅ ላይ የሚፈፀመ· ጥቃቶችን እንዲከላከልለት· ለነ·ረዲን ጥያቄ አቀረበ። ለዘመቻዎቹ የሚያስፈልገ· ወጪዎችን እንደሚሸፍንና የግብፅን አንድ ሦስተኛ ገቢ ለመክፈል ዝግጁ መሆኑን ለነ·ረዲን ማህመ·ድ ገለፀለት። መጀመሪያ ላይ ነ·ረዲን ወላወለ። ፈጥኖ አልወሰነም ነበር።ከጥቂት ጊዜያት በኋላ የየሩሳሌም ንጉሥ አል-ማሪክ ግብፅ ላይ ጥቃት ከፍቶ ዱር.ጋምን የማሸነፉ ዜና ተሰማ። ሻዊር ከነ·ረዲን ጋር በመሆን ያጠቃኛል ብሎ· የሰጋው ዱር.ጋም የነ·ረዲንን መልስ ሳይጠብቅ ከአል-ማረክ ጋር ለመሆንና ለአል-ማሪክ ግብር ለመክፈል ተስማማ። እዚህ ላይ ነ·ረዲን ሻዊርን ለመርዳት ተገደደ። ሻዊር ከዱር.ጋም ጋር ለሚያደርገው ትግል አሰዱዲን ሺርኩህን ሰጠው። አሰዱዲን በበኩሉ· የወንድሙን ልጅ ሰላሑዲን አስከትሉ· ሔደ። አሰዱዲን ዱር.ጋምን አሸንፈውና ሻዊር ዳግም የግብፅ ገዥ ለመሆን በቃ።

ነገር ግን ሻዊር ለነ·ረዲን የገባውን ቃል ኪዳን አልጠበቀም ነበር። እንዲያውም በተቃራኒው በሚስጥር ከየሩሳሌሙ· ንጉሥ ጋር አጋርነት· ፈጠረ። አሰዱዲንና ሰላሑዲን ሻዊርን ለመውጋት ተገደዱ። አ.ሒ.አ 559 (እ.ኤ.አ 1164) ላይ ከረመዳን እስከ ዙልሒጃ ባሉት· ጊዜያት· የሶሪያ ጦር ቡልቤስ ላይ በነበረው የመስቀለኞች ጦር እና በግብፅ ጦር ላይ ዘመተ። ነ·ረዲን የየሩሳሌሙ ንጉስ በግብፅ ጉዳይ የተወጠረበትን አጋጣሚ በመጠቀም በከፈተው ድንገተኛ ጥቃት ሐራምንና ጋኒያስን

የመሰሉ ጠንካራ ይዞታዎች ለመቆጣጠር ቻለ። በዚህ ምክንያት ንጉሥ አልማሪክ ግዛቱ አደጋ ላይ መውደቁ ስለተሰማው ሁለቱም ግብፅን ለቀው መውጣታቸውን እንደ ቅድመ ሁኔታ በማስቀመጥ ከአሰዱዲን ጋር ለመስማማት ተገደደ። በኑረዲንና በመስቀለኞች (ፍራንኮች) መካከል ግብፅን ለመጠቅለል የተደረገው የመጀመሪያው ትግል በዚህ ስምምነት ተቋጨ።

ግብፅ ላይ የተደረገው ትግል ሁለተኛ ምዕራፍ

አሰዱዲን ሺርኩህ ወደ ግብፅ በመሔዱ ብዙ ተጠቅሞ ነበር። ግብፅን ከላይ እስከታች በርብሮ አጠናት። መረመራት። መስቀለኞችን ማሸነፍ የሚችልባት ብቸኛ አገር ግብፅ በመሆኗ እርግጠኛ ሆነ። ቀጥሎ ሐሳቡን ለኑረዲን ገለጠለትና ለዘመቻ ፍቃድ ጠየቀ። ኑረዲንም ጥያቄውን ተቀበለው። በ562 (እ.ሐ.አ) በሺርኩህና በሰላሑዲን ለሚመራው ሁለተኛው ዘመቻ የሚያስፈልጓቸውን ነገሮች ሁሉ አደረገላቸው። የሶሪያ ጦር ወደ ግብፅ እያመራ መሆኑን የሰማው ሻዊር መስቀለኛ አጋሮቹን እርዳታ ጠየቀ። መስቀለኞች ሻዊርን ለመርዳት ተስማሙና ሁለቱ ጦሮች የግብፅ የላይኛው ክፍል በሆነችው ሙኒያ ላይ ገጠሙ። በ563 (እ.ሐ.አ) የሶሪያ ጦር በጠላቶቹ ላይ ድል ቀናው። ይህ ጦርነት የሰላሑዲን ጀግንነትና አይበገሬነት የተገለጠበት ጦርነት ነበር።

ቀጥሎ የሶሪያ ጦር ወደ ሰሜን በማቅናት ያለምንም ጠንካራ ተቃውሞ አሌክሳንደሪያን ተቆጣጠረ። አሰዱዲን የወንድሙን ልጅ ሰላሑዲንን የአሌክሳንደሪያ መሪ አድርጎ መረጠው። ይህ ኃላፊነት ለሰላሑዲን የመጀመሪያው ነበር። የስሜት ብስለቱን፣ አዕምሯዊ ብቃቱንና ጀግንነቱን ያሳይ ዘንድ ዕጣ ፈንታ ዕድል የሰጠችው ይመስል ነበር። አሰዱዲን ወደ አል-ፋስታት እና ወደ ካይሮ በሔደበት አጋጣሚ መስቀለኞች ከቤዛንታይን ወታደሮች ጋር በመተባበር አሌክሳንደሪያ ላይ ጥቃት ከፈቱ። በባህርና በምድር ከበቧት። የተከበበው የአሌክሳንደሪያ ህዝብ እጅ ለመስጠት ተቃርቦ ነበር። ሰላሑዲን ግን አጎቱ እስኪቀላቀለው ድረስ በዕናት ተከላከለ። የዚህ ምዕራፍ መዝጊያም ሁለቱም ወገኖች ግብፅን ትተው ለመውጣት መፈራረም ሆነ።